# ኬአይዲኤስ - የመዋዕለ ሕፃናት ጠቋሚ ገላጮች

## አርሊንግተን የህዝብ ትምህርት ቤቶች

## የመዋዕለ ሕፃናት የስራ ሂደት ሪፖርት



| የመዋዕለ ሕፃናት ስራ ሂደት ሪፖርት የነጥብ አሰጣጥ ኮድ | |
|---|---|
| **M- ያ- ያሟላል** | ሕፃኑ በተከታታይ የሚፈለግበትን የባህሪ ወይም የችሎታ መመዘኛ ያሟላል፡፡<br>ተማሪው ራሱን ችሎ ቁልፍ በሆኑ ጽንሰ ሃሳቦች እና መርሆዎች ላይ ያለውን ግንዛቤ ያሳያል። |
| **P- እ- እያዳበረ ነው** | ሕፃኑ ባህሪውን ወይም ችሎታውን በማዳበር ሂደት ላይ ይገኛል ፡፡<br>ተማሪው ዋና ዋና  ክህሎቶች፤ ስትራቴጂዎችን እና ጽንሰ ሃሳቦችን ወጥ በሆነ መንገድ ያሳያል ወይም ይተገብራል፡፡<br>ተማሪው መስፈርቶቹን በከፊል ያሟላል፡፡ |
| **B- ጀ ጀምሯል** | ሕፃኑ አንድ ባህሪ ወይም ክህሎት ማሳየት እየጀመረ ነው፡፡<br>ተማሪው ጽንሰ ሃሳቦችንና ክህሎቶችን መረዳት እየጀመረ ስለሆነ እነዚህ ተግባራት የተሟሉ እንዲሆኑ የመምህር ድጋፍ ያስፈልገዋል፡፡ |
| **N- ገ- ገና ነው** | ሕፃኑ ባህሪን ወይም ክህሎትን ማሳየት ገና አልጀመረም፡፡ |
| **NI- አይ- አልተዋወቀም** | ከክህሎት ጋር ገና አልተዋወቀም፡፡ |

የሪፖርት ካርዱ ጠቋሚዎች በግራ በኩል እንዲሁም ጠቋሚ መግለጫዎቹ በቀኝ በኩል ተዘርዝረዋል ፡፡

| **ማህበራዊ ዕድገት** | **ጠቋሚ መግለጫዎች** |
|---|---|
| ለመማር ጉጉት ያሳያል፡፡ | ጥያቄዎችን ይጠይቃል፣ ዕውቀቱን ያካፍላል እንዲሁም ለክፍል ውስጥ ተግባራት ፍላጎት ያሳያል፡፡ |
| አዳዲስ ነገሮችን ለመሞከር ፍላጎት ያሳያል | ለአዳዲስ የትምህርት ቤት ልምዶች በአወንታዊ መልኩ ይቀርባል፡፡ |
| በቡድን ተግባራት ውስጥ ይሳተፋል | በአጠቃላይና  በአነስተኛ የቡድን ተግባራት ውስጥ ተሳታፊ ነው፡፡ |
| ከሌሎች ጋር የመገናኘት ፍላጎት አለው ትህትናም ያሳያል | ሌሎች የሚሉትን ይሰማል ትኩረትም ይሰጣል፤ እርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ያግዛል፤ ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ አወንታዊ አስተዋጽኦ ያበረክታል ፡፡ |
| ችግሮችን ከሌሎች ጋር ተባብሮ ይፈታል | ከአዋቂዎች በሚሰጠው አነስተኛ ድጋፍ በመታገዝ ተገቢና አወንታዊ ቋንቋን ይጠቀማል፤ የሌሎችን መብት በመረዳት ነገሮችን ከሌሎች ጋር ይካፈላል፤ በተራ የሚከናወኑ ተግባራትን ተራውን ጠብቆ ይሳተፋል፡፡ |
| ኃላፊነትን ይቀበላል | የግል ንብረቶቹን በጥንቃቄ ይይዛል፤ ደንቦችን ይከተላል፤ በቅንነትም ይተገብራል፤ ሃላፊነትን ይቀበላል እንዲሁም የአንድ ሰው ድርጊት በሌሎች ላይ ስለሚኖረው ተጽእኖ ግንዛቤ አለው ፡፡ |

| **የስራ ልምድ** | **ጠቋሚ መግለጫዎች** |
|---|---|
| የራሱን ባህሪ ይቆጣጠራል | ተገቢ ውሳኔዎችን ይወስናል፤ ቅጽበታዊ ፍላጎቶቹን ይቆጣጠራል ለራሱና ለሌሎች አክብሮ አለው፤ ለዚህም ሁልጊዜ ተገቢውን ጥረት ያደርጋል ፡፡ |
| የክፍል ውስጥ መገልገያ መሳሪያዎቹን በአግባቡ ይይዛል | ክፍሉንና የትምህርት ቤቱን መገልገያዎች ለተፈለገው አላማ ያውላል ወይም  ይጠቀማል |
| የክፍል ውስጥ ተግባራትንና ደንቦችን ይከተላል | የክፍል ውስጥ እና የትምህርት ቤት የአሰራር ሂዶቶችንና ደንቦችን ያከብራል ፤ ይከተላል ፡፡ |
| ለውጦችንና ሽግግሮችን ተቀብሎ ያከናውናል | ተለምዷዊ ድርጊቶችን እና የጊዜ ሰሌዳ ለውጦችን ይቀበላል፤ ከአንድ ስራ ወደ ሌላው ተረጋግቶ ይሻገራል፡፡ |
| ብዙ ደረጃ ያላቸውን መመሪያዎች ይከተላል | ቢያንስ 3 የቅደም ተከል ደረጃ ላላቸው መመሪያዎች ገቢውን ምላሽ ይሰጣል፡፡ |
| ችግሮችን ለመፍታት ስትራቴጂያዊ ስልቶችን ይጠቀማል | በተግባር ወይም በቃል አስቸጋሪ ሁኔታዎችን የማረሚያ መንገዶችን ፈልጎ ያገኛል፡፡ |
| ራሱን ችሎ ይሰራል | ራሱን ለስራ ያዘጋጃል፤ በስራ ላይ ይሳተፋል፤ ስራውን በሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ያከናውናል ፤ ጊዜውን እና ጥሩን አመላካች የሆነ ውጤት |

| | |
|---|---|
| | ያስገኛል፡፡ |
| ለአንድ ተግባር ለተወሰነ ጊዜ አትኩሮት በመስጠት ይቆያል | ለተግባሩ ትኩረት ሰጥቶ ይቆያል፤ በአቋሙ ጸንቶ ተግባሩን ያጠናቅቃል፡፡ |
| በቡድን የሚሰጥ ትምህርትን ትኩረት ሰጥቶ ያዳምጣል | ታሪኮች ሲነገሩ ፣ ውይይቶች ሲደረጉ ፣ እና ወይም መመሪያዎች ሲሰጡ ሌሎችን ሳያውክ የመከታል ችሎታ ያሳያል፡፡ |
| የክፍል  ውስጥ መገልገያዎችን በአግባቡ ይጠቀማል | ለዕድሜው የሚመጥኑ ጥሩ የእንቅስቃሴ ችሎታዎችን ( ስዕል መሳል፣ ቀለም መቀባት፣ መቁረጥ ማጣበቅና ማተም) ይጠቀማል እንዲሁም እርሳስን በትክክል ይይዛል ፡፡ |
| በራስ ጥረት የሚከናወኑ ተግባራትን ራሱን ችሎ ይሰራል | ለአካላዊ ፍላጎቶቹና ንብረቶቹ ትኩረት ይሰጣል፣ ልብሶቹን ለመቆለፍ፣ ዚፑን ለመዝጋት፣ ለመክፈት እና ለማሰር ይሞክራል ፡፡ |

**ቋንቋ እና የማንበብና የመጻፍ ችሎታ**

| የቃል ቋንቋ | ጠቋሚ መግለጫዎች |
|---|---|
| በውይይትና በንግግር ጊዜ ምን እንደተባለ ያዳምጣል | ጥያቄ ይጠይቃል፣ ተረቶችን በድርጊት ያሳያል፣ ቃል አልባ በሆኑ የመግባባት ሂደቶች እና ወይም ውይይቶች አማካኝነት የተረዳቸውን ነገሮች ያሳያል፡፡ |
| ከሌሎች ጋር ለመግባባት ቋንቋን በአግባቡ ይጠቀማል | ሙሉ አረፍተ ነገሮችን ተጠቅሞ ይናገራል፣ ለመረዳት ቀላል የሆኑ ሀሳቦችንና ስሜቶችን ይገልጻል፡፡ |
| በቡድን ውይይት ጊዜ አስተዋጽኦ ያደርጋል | ተገቢውን ቋንቋ በመጠቀም ነገሮችን ለሌሎች ያሳውቃል፣ ያሳምናል ወይም የራሱን ሃሳብ ይገልፃል ፡፡ |

| የቃላት እውቀት | ጠቋሚ መግለጫዎች |
|---|---|
| ቤት የሚመቱ ቃላትን ያመነጫል | ለተሰጡት ቃላት አዳዲስ እና ቤት የሚመታ ሌላ ቃል ቀርባል ፡፡ |
| የቃላትን ድምፆች ሰምቶ ይለያል | በቃል መነሻና መጨረሻ ላይ የሚገኙ የፊደል ድምጾችንና የፊደል ምልክቶችን ያዛምዳል ፡፡ |
| ትልልቆቹንና ትንንሾቹን የእንግሊዝኛ ፊደላት ያውቃል ይለያል | የፊደላትን ተመሳሳይነት እና ልዩነት ይለያል፣ ትልልቆቹን እና ትንንሾቹን የእንግሊዝኛ ፊደላት በመለየት ያሳድጋል፡፡ |
| የፊደላትን ድምጾች ያውቃል ያሰማል | ለሚቀርብለት ማንኛውም ፊደል እና የፊደላት ጥምረት (ቸ፣ ውህ ፣ ሽ ዝ ) ትክክለኛ ድምጾችን ናገራል ፡፡ |

| ንባብ | ጠቋሚ መግለጫዎች |
|---|---|
| የግል ድምጾቹን ከጽሁፎቹ ጋር ያገናኛል | ራሱን ከግጥሞች እና ከተረቶች ጋር ያገናኛል ፡፡ |
| የልብ ወለድ እና የኢ-ልብ ወለድ ዝርዝር ታሪኮችን ያስታውሳል | በልብ ወለድ እና በ ኢ-ልብ ወለድ ታሪኮች ውስጥ ስለሚገኙ ገጸ ባህሪያት ፣ ድርጊቶች ፣ ክስተቶች እና ጭብጦች ሚቀርቡ ጥያቄዎችን ይመልሳል ፡፡ |
| ስለ ህትመት ጽንሰ ሃሳቦች ግንዛቤ ያሳያል | የመጸሀፍን ፊት እና ጀርባ ይለያል፣ ከግራ ገጽ ወደ ቀኝ ገጽ ይገለብጣል፣ የታተሙ ጽሁፎችን እና ስዕሎችን ይለያል፣ በፊደል እና በቃል መካከል ያለውን ልዩንም ያውቃል፡፡ |
| የተነገሩ ቃላትን ከተጻፉት ጋር አንድ በአንድ ያዛምዳል | ከሚነበበው ጽሁፍ ውስጥ ቃላትን ለይቶ ያሳያል፣ የተሰጠውን ቃል ከ ዐረፍተ ነገር ውስጥ ለይቶ ያወጣል፡፡ |
| ቀላል እና ከፍተኛ ድግግሞሽ ያላቸውን ቃላት ያነባል | የራሱን እና የእኩዮቹን ስም ለይቶ ያውቃል፣ የአካባቢ ህመትን ጨምሮ የተዘወሩ ቃላትን ማንበብ ጀምሯል፡፡ |
| ሊገመት የሚችል፣ የታወቀ እና ሊፈታ የሚችል ጽሁፍን ራሱን ችሎ ያነባል | ሊገመት ሚችል እና ተደጋጋሚ ቋንቋዊ አካሄድ ያላቸውንብዙ መፃህፍት ያነባል፡፡ |

| መጻፍ | ጠቋሚ መግለጫዎች |
|---|---|
| የሚያሰላስላቸውን ነገሮች እና ሃሳቦች በወረቀት ላይ ይጽፋል | ሀሳቡን የሚገልፁለትን ዝርዝር ሥዕሎች ይስላል ፣ ፊደላን እና በአጠራራቸው የተፃፉ ቃላትን በመጠቀም ስለ ልምዶቹ፣ ተረቶች፣ ሰዎች፣ ነገሮች፣ ወይም ስለ ክስተቶች ይጽፋል፡፡ |
| ለተለያዩ ዓላማዎች ይጽፋል | ጆርናሎችን፣ ኢ-ልብ ወለዶችን፣ ዝርዝሮችን፣ ካርዶችን፣ ተረቶችን፣ መዝገቦችን  ወ.ዘ.ተ ይጽፋል፡፡ |

| | |
|---|---|
| በአንድ ርዕስ ስር በርካታ ዓረፍተ ነገሮችን ይጽፋል | በአንድ ሃሳብ ስር ከ ሁለት እስከ ሶስት ዐረፍተ ነገሮች ይጽፋል፡፡ |

**ሒሳባዊ አስተሳሰብ**

| ቁጥር እና የቁጥር ግንዛቤ | |
|---|---|
| ስለ ተከታታይ ቁጥሮች ያለውን ግንዛቤ ያሳያል | በአንድ ስብስብ ውስጥ የሚገኙ አባላትን በቃሉ ይቆጥራል ( እስከ አስራ አምስት)፣ እንዲሁም ተጓዳኝ ቁጥሮችን ይለያል ይጽፋል፣ ወደ ፊት እስከ 100 እንዲሁም ወደ ኋላ ከ አስር ጀምሮ ይቆጥራል፣ በ 5 እና በ 10 ልዩነት እስከ 100 ድረስ በመቁጠር ሂደቱን ይለያል፡፡ |
| የበዛ ፣ ያነሰ ወይም እኩል መጠን ያላቸው አካላት ስብስብ ይለያል ይፈጥራል | የ 1 ለ 1 ጥምረትን በመጠቀም የአንድን ስብስብ አባላት ከሌላ ስብስብ አባላት ጋር ያዛምዳል ፣ ይበልጣል ፣ ያንሳል ወይም እኩል ይሆናል የሚሉትን ምልክቶች በመጠቀም 15 ወይም ከዚያ ያነሱ አባላት ያሏቸውን ስብስቦች ነጻጽራል እንዲሁም ያመለክታል ፡፡ |
| ቁሳቁሶችን በመጠቀም እስከ 15 ድረስ ያሉቁጥሮችን ማሳየት ይችላል | አንድን ቁጥር ለማሳየት የተለያዩ ዘዴዎችን ይጠቀማል 9 በአንድ እጅ ላይ ያሉ አምስት ጣቶችን ፣ አምስት የታሊ ምልክቶችን ፣ አምስት ዕቃዎችን ለምሳሌ 2 ቀይ እና 3 ሰማያዊ ወ.ዘ.ተ ) ይጠቀማል ፡፡ |
| የመቁጠሪያ ቁጥሮችን በመጠቀም የአንድን ነገር አቀማመጥ ይለያል | የአንድን እቃ አቀማመጥ ከአንድ እስከ አስር ከግራ ወደ ቀኝ ፣ ከቀን ወደ ግራ ፣ ከላይ ወደ ታች እና ወይም ከታች ወደ ላይ በመቁጠር ያሳያል ፡፡ |

| ማስላት እና መገመት | |
|---|---|
| እቃዎችን በመጠቀም እስከ 10 የሚደርሱ ሁለት ሙሉ ቁጥሮችን ይደምራል ይቀንሳል | ሁለት ስብስቦችን በማዋሃድ ወይም በማገናኘት ድምራቸውን ይለያል ፡፡ ከአንድ ስብስብ ውስጥ የተወሰነውን ክፍል በማንሳት ወይም በመለየት የመቀነስን ውጤት ይለያል ፡፡ ሞዴሊንግ እና የተለያዩ ፕሮብሌሞችን የመፍቻ ስትራቴጂዎችን ይጠቀማል ፡፡ |

| መለካት | |
|---|---|
| እንደ ርዝመት ፣ ክብደት ፣ ጊዜ እና የሙቀት መጠን ያሉ ተለኪዎችን ይለያል ይገልጻል | መለኪያ መሳሪዎችን ይለያል ለርዝመት ( ማስመሪያ ) ፣ ለክብደት ( ሚዛን )፣ ለጊዜ ( ዲጂታል እና አና ሎግ ሰዓት ለቀን መቁጠሪያ ፣ ቀን ወር እና ወቅት) እንዲሁም ለሙቀት መጠን መለኪያ ( ቴርሞሜትር ) |
| አንድ ፣ አምስት ፣ አስር እና ሃያ አምስት ሳንቲሞችን እና ያላቸውን ዋጋ ይለያል | አንድ ፣ አምስት ፣ አስር እና ሃያ አምስት ሳንቲሞችን እና ያላቸውን ዋጋ ይለያል ፡፡ በድምሩ የአስር ሳንቲም ዋጋ ያላቸውን ባለ አንድ ሳንቲሞች እና ወይም የአምስት ሳንቲሞችን ስብስብ ዋጋ ይገልጻል ፡፡ |

| ጂኦሜትሪ | |
|---|---|
| ባለ ሁለት ገጽታ ቅርጾችን ለይቶ ያውቃል፣ ይስላል፣ ይገልፃል መጠናቸውንም ያነጻጽራል ፡፡ | የክብ፣ ሶስት ማእዘን፣ እኩል አራት ማእዘን እና አራት ማእዘን ምስሎችን ይስላል ይለያል፣ የጎናቸውን እና የጠርዞቻቸውን ቁጥር ጨምሮ የየምስሎቹን ባህሪያት ይገልጻል፣ በቦታው ላይ ያላቸውን አቀማመጥ እና አቅጣጫ ከግምት ውስጥ ሳያስገባ ከአንጻራዊ መጠናቸው እና ቅርጻቸው በመነሳት እነዚህን ምስሎች ያነጻጽራል ይመድባል፡፡ ከ ላይ፣ ከታች እና ከጎን የሚሉትን ቃላት በመጠቀም አንዱ እቃ ከሌላው አንጻር ያለውን አቀማመጥ ይገልጻል፡፡ |

| የመሆን እድልና ስታቲስቲክስ | |
|---|---|
| መረጃዎችን ( በመቁጠር እና በመደብ በመከፋፈል) ያደራጃል ፣ በግራፍ ለተቀመጡ መረጃዎች መልስ ይሰጣል ፡፡ | ምድቦችን፣ ፒክቶግራፍን፣ የቁም ግራፍን ወይም ሰንጠረዥን ተጠቅሞ መረጃዎችን ያደራጃል፣ ያሳያል እንዲሁም ይተረጉማል ፡፡ |

| አወቃቀር ፣ ተግባር እና አልጄብራ | |
|---|---|

| | |
|---|---|
| ዕቃዎችን ከፋፍሎ ይመድባል፣ መከፋፈያ ደንቡንም ያስረዳል | የእቃዎችን ባህሪ መሰረት በማድረግ ከፋፍሎ ይመድባል፣ የእቃዎቹ ስብስብ በሚኖራቸው የጋራ ባህሪ መሰረት በሶስት ምድብ ይከፋፍላል (ለምሳሌ ለትንሽ ፣ መካከለና እና ትልቅ መጠን ) |
| ዕቃዎችን ተጠቅሞ ሂደቶችን ይለያል፣ ይገልጻል፣ ይዘረጋል እንዲሁም ይፈጥራል ፡፡ | የተለመዱ ዕቃዎችን፣ ድምጾችን እና ወይም እንቅስቃሴዎችን ተጠቅሞ ዋና ዋና ተደጋጋሚ ሂደቶችን ያጤናል፣ ይገልጻል ፣ ይገልጻል እንዲሁም ይዘረጋል፡፡ |

## ማኅበራዊ ጥናቶች ፣ ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ

| ማኅበራዊ ጥናቶች | |
|---|---|
| ታሪካዊ ክስተቶችን፣ ሰዎችን፣ አፈ- ታሪኮችን እና የታሪኮችን ምሳሌዎች ይረዳል፡፡ | ታሪካዊ ክስተቶችን ( የምስጋና ቀን ወ.ዘ.ተ )፣ ሰዎችን ( ማረቲን ሉተር ኪንግ ፣ ጆርጅ ዋሺንግተን እና አብርሃም ሊንከንን ፣ ፖካሆንታስ ፣ ወ.ዘ.ተ) እንዲሁም አሜሪካውያን የታሪክ ሰዎችን እና ታሪኮችን ለይቶ ያውቃል፡፡ |
| ካርታዎችን እና ሉሎችን በመጠቀም ትክክለና እና አንጻራዊ የቦታዎችን መገኛ መለከታል፡፡ | ካርታ የነገሮች መገኛ ቦታን ለማሳየት የሚገለግል ምስል ሲሆን ሉል ደግሞ ክብ የሆነ የመሬት አምሳያ ወይም ሞዴል መሆናቸውን ይረዳል፡፡ |
| ሰዎች ገንዘብን እና ፍላጎትን የተመለከቱ ኢኮኖሚያዊ ምርጫዎችን እንደሚያደርጉ ይረዳል፡፡ | በሰዎች የሚከናወኑ ስራዎች ቀላል መግለጫዎች እና ስማቸውን ያዛምዳል ፣ ሰዎች ሚፈልጉትን ነገር ሁሉ ለማግኘት ስለማይችሉ ምርጫ የሚያደርጉ መሆኑን ይረዳል፡፡ |

| ሳይንሳዊ አስተሳሰብ | |
|---|---|
| ተግባራዊ ምርምርን በመጠቀም ለጥቄዎች መልሶችን ይፈልጋል | ማግኔት፣ ቁስ አካል፣ ህይወት ያላቸው ነገሮች ፣ ውሃ እንደገና መጠቀም ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉትን በመጠቀም ዳሰሳዎችን በማካሄድ ልያቄዎች የሚሆኑ መልሶችን ይፈልጋል፡፡ |
| የስሜት ህዋሳቱን እና ሳንሳዊ መገልገያዎችን ተጠቅሞ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ የአስተውሎት ጥናቶችን ያካሂዳል፣ ንጽጽሮችን ያደርጋል ፡፡ | የማየት ፣ የመስማት ፣ የመንካት ፣ የማሽተት እና የመቅመስ ስሜቶቹን በመጠቀም ያስተዋላቸውን ነገሮች ይገልጻል ፤ ማጉያዎችን ፣ ቴርምሜትሮችን እና ሚዛኖችን ይጠቀማል ፤ የሚመሳሰሉ እና የሚለያዩ ነገሮችን ይገልጻል (ጥላዎችን፣ የአየር ጠባይን፣ አወቃቀሮችን እና ዑደቶችን፣ በጊዜ ሂደት ውስጥ የሚፈጠሩ ለውጦችን ወ.ዘ.ተ፡፡ |
| በማስተዋል እና በድርጊት ላይ የተመሰረተ እውቁን ለሌሎች ያጋራል፡፡ | ቋንቋን፣ ስዕልን፣ ተግባራዊ ማሳያን እና ጽሁፍን ይጠቀማል፡፡ |

| ቴክኖሎጂ | |
|---|---|
| መረጃዎችን ለማግኘት እና ችሎታውን ለማዳበር የሚያስችሉ የተሌዩ መሰረታዊ የቴክኖሎጂ እውቀቱን በግባር ያሳያል | የማውዝ ፣ ኪቦርድ፣ ማተሚያ፣ መልቲሚዲያ፣ መሳሪዎችን የጆሮ ማዳመጫዎችን ትክክለኛ አጠቃቀም በተግባር ያሳያል፣ እንደ መጻህፍት እና ሶፍትዌሮች ያሉ አሳታፊ የመልቲ ሚዲያ መረጃዎችን ይጠቀማል፤ መሳሪያዎችን እና ሃብቶችን በትንቃቄ መጠቀምን ይረዳል በተግባርም ያሳያል |

## ሥነ ጥበብ ፣ ሙዚቃ እና የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት

| ሥነ ጥበብ | |
|---|---|
| ተለያዩ የስነ ጥበብ መገልገያዎችን በመጠቀም ፈጠራዊ ሃሳቡን ይገልጻል | ስነ ጥበባዊ ውጤቶችን ለማዘጋጀት የስዕል ቀለሞችን፣ ማርከሮችን፣ የጭቃ ቀለሞችን፣ መቀስ፣ ወረቀት እና የሸክላ አፈርን ይጠቀማል፡፡ |
| የጽንሰ ሃሳብ እውቀቱን በተግባር ያሳያል | መስመር፣ ቅርጽ፣ ቀለም በመጠቀም አንድን ሃሳብ ለሌሎች ያስተላልፋል፤ ሰዓሊዎች መስመር ፣ ቅርጽ እና ቀለም እንደሚጠቀሙ ይረዳል፡፡ |
| ቴክኒካዊ የአሰራር ደት ግንዛቤውን በተግባር ያሳያል ( የተለያዩ የመረጃ ማስላለፊ ዘዴዎችን በመጠቀም ) | ዝርዝር ቴክኒኮች እና በእያንዳንዱ መረጃ ማስተላለፊያ የሚገኙ የአሰራር ሂደቶች ስነ ጥበባዊ ሃሳቦችን በብቃት ለማስተላለፍ እንደሚጠቅሙ ይረዳል፡ ፡ |
| የክፍል ውስጥ ደንቦችን ያከብራል ይከተላልም | የስነ ጥበብ መሳሪያዎችን የክፍል ውስጥ የአጠቃቀም ስነ ስርዓት፣ ተለምዷዊ የጽዳት ስራዎችን፣ በተራ ለሚሰሩ ስራዎች ተራ መጠበቅን፣ ስነ ጥበባዊ ቋንቋን በመጠቀም ስለ ስነ ጥበብ መነጋገርን ይረዳል፡፡ |

| ሙዚቃ | |
|---|---|
| በመዝሙር ውስጥ በንቃ ይሳተፋል ፡፡ | የተለያዩ የድምጽ አጠቃቀሞችን ይረዳል፣ ሹክሹክታ፣ መናገር፣ መዘመር፣ መጮህ፣ የመዘመሪያ ድምጾችን የመጠቀም ችሎውን በተግባር ያሳያል፤ በዜማ ውስጥ ያሉ የድምጽ ውፍረቶች እና ቅጥነቶች ከፍ እና ዝቅ የሚል መስመር ሊፈጥሩ እንደሚችሉ ይረዳል፡፡ |
| ውዝዋዜ በማድረግ የክፍል ውስጥ የሙዚቃ መሳሪያዎችን በመጫወት በሙዚቃዊ ምት ተግባራት ላይ ንቁ ተሳትፎ ያደርጋል፡፡ | ወጥ የሆነ ወይም ያልተዘበራረቀ ምትን የመፍጠር ችሎታውን በተግባር ያሳያል፤ በክፍል ውስጥ የምት የሙዚቃ መሳሪያዎች ላይ ተገቢውን ቴክኒክ መጠቀም እንደሚችል በተግባር ያሳያል፡፡ |
| የሙዚቃን ጽንሰ ሃሳብ ይረዳል | ከፍተኛ / ዝቅተኛ ድምጾችን ፤ ለስላሳ/ ጉልህ ሁኔታን፤ ረጋ ያለ/ ፈጣን ሙዚቃዊ ምትን በተግባር ያሳያል፡፡ |
| የክፍል ውስጥ ደንቦችን ያከብራል ይከተላልም | እንዴት ተራውን መጠበቅ፣ መመሪዎችን ማድመጥ እና መከተል እንዳለበት፣ የክፍል ውስጥ መሳሪያዎችን እንዴት በጥንቃቄ መያዝ እንዳለበት እና ተገቢውን ቴክኒክ መተቀም እዳለበት ይረዳል፡፡ |

| የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት | |
|---|---|
| መሰረታዊ የአካል እንቅስቃሴዎችን ያከናውናል | እንቅስቃሴያዊ የሆኑ እና እንቅስቃሴያዊ ያልሆኑ ችሎታዎችን እንደ መራመድ፣ መዝለል፣ ዱብ ዱብ ማለት፣ ቀላል ዝላይ መዝለል፣ መሮጥ፣ እንጣጥ ማለት፣ መጠማዘዝ ፣ ማጎንበስ ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉትን በሚያከናውንብ ወቅት የተለያዩ አቅጣጫዎችን፣ ደረጃዎችን፣ መስመሮችን እና ጥረቶችን በመጠቀም ለእድሜቅ የሚመጥኑ እንቅስቃሴዎችን እንዲሁም የዓይን እና እጅ የዓይን እና እግር ጥምረትን በሰውነት ማጎልመሻ መሳሪያዎች አማካይነት በተግባር ያሳያል፡፡ |
| በጠንካራ የአካል እንቅስቃሴዎች ውስጥ ይሳተፋል | አካላችን ለጠንካራ እና ቀላል አካላዊ እንቅስቃሴዎች የሚኖረውን ምላሽ ለመረዳት ከመጠነኛ እስከ ጠንካራ የአካል እንቅስቃሴዎች ለአጭር ጊዜ ይሳተፋል፡፡ |
| የትብብር ስራ ላይ በተግባር ይሳተፋል ለራሱም አክብሮት አለው | እስፖርታዊ ጨዋነትን፣ የመጋራት ችሎታን፣ ተባባሪነትን ፣ በሰውነት ማጎልመሻ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ሌሎችን የማክበር እና ደህንነታቸውን የመጠበቅ ችሎታውን በግባር ያሳያል፡፡ |
| የክፍል ውስጥ ደንቦችን ያከብራል ይከተላልም | መሳሪያዎችን በጥንቃቄ የመያዝ፣ የደህንነት ባህሪን፣ በየተራ የመስራት፣ አዋቂዎች የሚሉትን የማድመጥ እንዲሁም በሰውነት ማጎልመሻ እንቅስቃሴ ወቅት መመሪያዎችን የመከተል ችሎታውን በተግባር ያሳያል፡፡ |

| ኤፍ ኤል ኢ ኤስ (ሁሉም ትምህርት ቤቶች አይደሉም) | |
|---|---|
| ከተለምዷዊ ነገሮች የሚመነጩ አጠር ያሉ ስሜቶችን ይረዳል፡፡ | የተለምዷዊ ስሜቶች እውቀቱን በተግባር ያሳያል፡፡ በትክክለኛው እንቅስቃሴም መልስ ይሰጣል፡፡ |
| መሰረታዊ ሰላምታዎችን ፤ መልካም ጠባይ ማሳየት እና የክፍል ውስጥ መመሪያዎችን ይገነዘባል ፡፡ | መሰረታዊ ሰላምታዎችን እና የአንድ ደረጃ ትእዛዝን ይረዳል ይጠቀማልም፡፡ |
| መሰረታዊ ድምጾችን በትክክል ይናገራል | ትክክለኛውን አነጋገር በተግባር ያሳያል፡፡ |
| መሰረታዊ ሰላምታዎችን መስጠት፣ ደህና ሁኑ ማለት መልካም ጠባይ ማሳየት ይችላል፡፡ | መሰረታዊ ሰላምታዎችን፣ ደህና ሁኑ ማለትን፣ መልካም ጠባይ ማሳየትን ይረዳል ይጠቀማልም፡፡ |
| ቀላል እና የሚታወሱ ዐረፍተ ነገሮችን ይፈጥራል፡፡ | ቀላል እና ሊታወሱ የሚችሉ ከተለምዷዊ ነገሮች የሚፈጠሩ ዐረፍተ ነገሮችን ይናገራል ፡፡ |